7. ሀገራቱ በኢምፔርያሊስቶች ላይ ጥገኛ ከመሆን መላቀቅ አለበት ስለዚህ፣
ሀ/ በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተ በሀገራቱ ስም የተደረገ የዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ውሎች ሁሉ ባስቸኳይ እንዲሠረዙ፡፡
ለ/ የውጭ አገር ጦር ሰፈሮች ሁሉ እንዲፈርሱ፣ የውጭ አገር የጦር አማካሪዎች ሁሉ ካገር እንዲባረሩ፡፡

የላብ አደሩ መደብ ግንባር ቀደም የሆነው ኢ.ሀ.አ.ፓ. ከላይ የተጠቀሱት የጊዜው ጥያቄዎች እንዲፈጸሙ በከፍተኛ አብዮታዊ ቆራጥነት ይታገላል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጥያቄዎችና ሌሎች መሠረታዊ የሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ጥያቄዎችና ሌሎች መሠረታዊ የሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ጥያቄዎች እንዲፈጸሙና አብዮቱ በመቀጠሉም ግቡን እንዲመታ የሚችሉ ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች ወደራቸውን ስለሚገነዘቡ በተወሰነ የመነሻ ፖለቲካ ፕሮግራም መሠረት ፀረ ኢምፔርያሊስት፣ ፀረ ፊውዳልና፣ ፀረ የቢሮ ከበርቴ ኃይሎች ሁሉ በአንድ ጠንካራ ዲሞክራሲያዊ የህብረት ግንባር ሥር እንዲተባበሩ ጥሪ ያደርጋል፡፡ ይህ የህብረት ግንባሩ ለማንኛውም የግንባሩ አባል ለሚሆን የፖለቲካ ድርጅት ቡድን ግለሰብም ሁሉ የድርጅት ነፃነት /የመደራጀትና የመሰብሰብ/ የፖለቲካ ፓርቲ ንና የርእዮተ ዓለም ዝንባሌውን በይፋ የመግለጽ መብት በተግባር እንደሚያረጋግጥ ሁኖ ይደራጃል፡፡

*በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር /የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን አባል/ እንደገና በጽሕፈት መኪና /ታይፕ/ ተመቶ የ[illegible]